ቁጥር - ኢህ62/11/15342
: [illegible] 10.2017

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ለጋምቤላ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ጋብዴን)**

**ጋምቤላ**

የጋምቤላ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ጋብዴን) በ2016 ዓ.ም ከቦርዱ የሚሰጠውን ድጋፍ ለማግኘት የሴት አባላት ቁጥር እና የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር በቃለ-መሐላ በተደገፈ መረጃ ለቦርዱ አቅርቦ ገንዘብ መውሰዱ ይታወሳል።

ፓርቲዉ መጀመሪያ ለቦርዱ በቃለ-መሐላ ያሳወቀው የሴት አባላት ቁጥር 32,453፣ የአካል ጉዳተኛ ብዛት 1,123 እና የካል ጉዳተኛ አመራር 3 ነበር፤ ቦርዱ ከዚህ በላይ በፓርቲው የቀረቡለትን የአመራር እና የአካል ጉዳተኛ ቁጥር በተመለከተ ፓርቲው ማስረጃ እንዲያቀርብለት ጠየቀ። ይሁንና ፓርቲው አስቀድሞ ካቀረበው ቁጥር በጣም ዝቅ ያለ የሴት አባላት ብዛት 1,225፣ አካል ጉዳተኛ አባላት ብዛት 13፣ አካል ጉዳተኛ አመራር ብዛት 1 በማለት ለቦርዱ አሳወቀ።

ይህንም አሀዝ የሚደግፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠየቀ አላቀረበም። ፓርቲው መጀመሪያ ለቦርዱ በአቀረበዉ ማስረጃ መሰረት በሴት አባላት ቁጥር ልክ ብር 26,539፣ በአካል ጉዳተኛ አባላት ልክ ብር 17,600 እና በአካል ጉዳተኛ አመራር ልክ ብር 226,744.18 በአጠቃላይ ብር 270,883.18 ለወሰደው ገንዘብ በተጤቀው መሰረት ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠየቀ እስካሁን የተጠየቀውን ማስረጃ አላቀረበም።

በመሆኑም ቦርዱ ፓርቲው የወሰደውን ገንዘብ ተመላሽ እንዲያደርግ እና ፓርቲዉ ታግዶ በአዋጅ ቀጥር 1162/2011 አንቀጽ 98(1(ሠ)) መሰረት ሊሰረዝ የማይገባበትን ምክንያት ያቅርብ ተበሎ በቦርዱ ተወሰነ። ይሁንና መከላከያ መልሱን አላቀረበም፣ ገንዘቡንም ለቦርዱ ገቢ አላደረገም።

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

ስለዚህ ፓርቲው በቦርዱ የተጠየቀውን መረጃ እንዲሁም መከላከያ መልሱን ካለማቅረቡም በላይ እንዲመልስ የታዘዘውን አለማቅረቡ እና በሴት፣ በአካል ጉዳተኛ አባል እና አመራር ልክ የወሰደውን ብር 270,883.18 አልመለሰም።

በመሆኑም በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ዓ/ም አንቀጽ 78(1(ሀ፤ለ)፣ 4)፣ አንቀጽ 79(1) በጣሰ መልኩ የተንቀሳቀሰ ስለሆነ ቦርዱ በአንቀጽ 68(7) በተሰጠው ስልጣን መሰረት በአንቀጽ 98(1)(ሠ) መሰረት ፓርቲዉ እንዲሰረዝ አመራሮቹም በዚህ ፓርቲ ስም ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ቦርዱ ወስኗል።

እንዲሁም ፓርቲው የተሰጠውን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እንዳላዋለዉ ግምት ስለሚወሰድ አንቀጽ 106(1(ለ)) መሰረት አመራሮቹ አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ እንዲጠየቁ፤ ፓርቲው የወሰደውን የድጋፍ ገንዘብ በተመለከተ በአንቀጽ 106(2) እና በፍትሐ-ብሔር ሕግ ስለአላግባብ መበልፀግ በተደነገጉ ህጎች መሰረት ተከሶ እንዲመልስ በማለት ህዳር 12 ቀን 2017 ዓ/ም ቦርዱ የወሰነ መሆኑን በአክብሮት ያሳውቃል።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board

**<u>ግልባጭ</u>**

- ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት
- ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ህግ ክፍል

**<u>አዲስ አበባ</u>**